<u>**ሰዉ ኣየሁ እንደ ኖኅ በፓሊካን ሰፈር**</u>

*ለፕሮፌሰር ኤፍሬም ይስሓቅ  ክብርና መስጋና የተገጠመ*
*በላእከ ጥበባት ፍጹም ገብረ ሕይወት ዘብሔረ ዋጅራት/ካናዳ*

ጦቢያ ላይ ድብ ፀር ነግሶ
የራእይ ምንጭ ሀበቷ በዱላ ተገምሶ
በመሳፍንት ዘመን የነበራት አጥታ
ኣህጉራትም ረስዋት  ጨለማዉስጥ ገብታ፡

‘ኢይኃድጋ ለሃገር…..’ይፈጸም ዘንድ ቃሉ
 የተስፋ ኮከቦች ባንድ ወቅት ብቅ ኣሉ
 ኣፄ ናኦድ’ና ከሀገረ አግኣዝያን ሞኀሳዊዉ ዕዝራ
 ኢየሩሳሌም ደርሶ ኣቋርጦ ሰሃራ
 ልምድ ጥበብ ሸምቶ በአበሻ ምድር የዘራ

 ኣፄም ከያገሩ ጥበብ ሊያስተምሩ ጠርቶ ያስመጣቸዉ
 በይፋ መስክሮ
 ኣዱም የዕዝራን ያህል  አለመስራታቸዉ
 ታላቅ የራእይ ሰዉ በሂወቱ ዘመን
 አምላክ  ስላሳየዉ ኣመሰገነ ኦ ን ።

 የናኦድ ልብ ተኪ ያኔ ቢነግሥልን
 የዕዝራንም ጥበብ ያኔ ቢስፋፋልን
 አሁን የት በደረስን?

 ስብሰሃት ለኢህኣዴግ ለጀገኖች ሰማእታት
 በፍላጎት ኣንድነት ለእድገት ምንነሳበት
 የኀዳሴ ዘመን እዉን ሳደረጉት
 ትመክህትና እልህ በምድረ ዲያስፖራ
 ሳይሆኑ ከመምሰል ከማብዛት  ፉከራ
 ኣእመአሮን ከማድረግ የእልሀ ኀተራ
 ኣሻለንም ወይ
 ኣብረን ብንነሳ ለግንባታ ስራ

 ያገር በቻ ሳይሆን የዓለምን  ምስጢር
 ጠንቀቀዉ ሚያዉቁ የምሁራን መምህር
 A+ ለመለስ ብለዉ የሰጡ’ለት ለታሪክ ምስክር
 ባህርይዎ ጥልቅ መራኝ ሊቁ ፕሮፌሰር
 ሰዉ ኣየሁ እንደ ኖኅ በፓሊካን ሰፈር
 አበቁኝ ለመፃፍ የምስጋና መዝሙር

**ትዉልድ ሲያመሰግነዎ ይኖራል!!**